# ላም አለኝ በሰማይ፤ ወተትዋንም አላይ

ከአቦ አራዳ አባ ሻውል

## እ.አ. ጥር 5 ቀን 2014

### *መግቢያ*

ከዚህ በፊት ስለ ሁለት መጽሐፍት አስፈላጊነትና ወቅታዊነት በስፋት ተተችቶና ተወድሶ አንብቤዋለሁ። እነሱም አንደኛው ፤ *የአሲንባ ፍቅር* በካሳሣይ አብርሃ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ *ታወርኢንዘስካይ* በእንግሊዘኛ - “tower in the sky” በሚል በወይዘሪት ሕይወት ተፈራ የተደረሱ ነበሩ። በወቅቱ ስለ አሲምባ ፍቅር ያለኝን አስተያየት ሰጥቻለሁ።

በሳንሱር ምክንያት ማንም ድኅረ ገጽ ያወጣው ያለ አይመስለኝም ከኢትዮ-ላዮን (Ethiolion.com) በስተቀር። ***አሁንም አመራር[ά] በኢትዮጵያ ፣ ዲሞክራሲያ በኤርትራ እና ዴሞክራሲያ በኤትዮጵያ[έ] እያልኩ ስለ አስምባ ፍቅር ደራሲ አስተያየቴን እንድታነቡ እጋብዛለሁ።***

በዛሬው ጽሑፌ ደግሞ ስለ ወ/ት ሕይወት የጻፈችውን አስተያየቴን ለመስጠት ነው። ጽሑፉ በእንግሊዘኛ ስለሆነ አስተያየት መስጠቱ በእንግሊዘኛ ባመቸን ነበር፤ ነገር ግን እንግባባለን የሚል ተስፋ ስላለኝ ትችቴን እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ።

## ስለ ምልመላ

ጸሐፊዋ ከየት ተነስታ ወዴት እንደደረሰች በሚገባ ገልጣለች። ከግል ዲሞክራሲ እስከ የጋራ ዴሞክራሲያ በሚገባ ገብቷታል፣ አውቃለችም፣ በተግባርም ለማዋል በሚገባ ታግላለች። እንዲያውም አስተማሪዋን በፈጣን እርምጃ አልፋ ለጽናተ ምሁር አካል በቅታለች። እንዲያውም በንድፈ-ሐሳብ (ተዎሪ) ከጌታቸው ማሩ በልጣ በጠቀሰቻቸውና እንዲሁም በአጻጻፏ የንቃቷን ችሎታ በግልጽ አሳይታለች። ጌታቸው ከምህንድስና አልፎ ያነበባቸው መጽሐፎች ቀኖናዊ ይዘት የበዛባቸው ነበሩና ነው። በዚህ ምክንያት ነበር ደግሞ ጌታቸው የጴንጤ ተከታይ ሳይሆን አይቀርም ተብሎ የተነገረው። ጴንጤ ማለት “ድግግሞሽ” ለማለት እንጂ ከሃይማኖት ጋር የተዛመደ ጉዳይ አልነበረም።

በሌላ አነጋገር ወ/ት ሕይወት በግልዋ በጌታቸው አማካይነት ነቅታ፣ በሊጉ ተደራጅታ በኢሕአፓ የታጠቀች ጀግና ነበረች አሁንም ነች። ኢሕአፓዊ

---

[ά] አመራር ማለት ከአስተዳደር የተለየ ያለፈውን ሳይሆን መጪውን የሚያመለክት ጥንሰና ንድፈ ሀሳቦችን ያመለክታል
[έ] ኤትዮጵያ ማለት ሁሉን ነገር፤ ግልበጣውም ሆነ ብተናውን አልፋ በአንድነት በግልም በጋራም ለምትኖር

ምልመላም በጅምላ ሳይሆን በግል እንደ ነበረና ሂደታዊ መሆኑን ከደራሲዋ ታሪክ በሚገባ ለመረዳት ይቻላል።

## ስለ ፍቅርና እምነት

እንደሚታወቀው ግላዊ ፍቅርና ሕዝባዊ ፍቅር ለየቅሉ ነው። ወ/ት ይሕወት ሁለቱንም ለይታ የምታውቅ ነች። አስተማሪዋ ግን ይኸንን ልዩነት እንደማያውቅ በብዙ ነገረ-ጉዳዮች ታይተዋል። ከብዙ በጥቂቱ ጌታቸው እንደነ ብርሃነ መስቀል ዓይነቶቹ የፍትወተ-ስጋ ችግር ስለነበረባቸው ማለትም "ሊበሬትድ" ወይም በወ/ት ሕይወት አነጋገር "ኢማኒሲፔትድ" ስላልነበሩ ለችግርና ለሞት በቁ። የጌታቸው መልማዮች ሆን ብለው በተግባር ለመፈተን ወይንም እንዲነቃ በማለት ሳይሆን አይቀርም መጀመሪያውኑ "ጆሊ" ተማሪ ሕይወት ተፈራን ያስተዋወቁት። የተፈራውም አልቀረ ከመለመላት "ጆሊ" ተጣብቆ ቀረ። የፓርቲው አመራር ቀርቶ የተራ አባሎች አሠራር እንኳ አልተከተለም ነበር። በወቅቱ ፍትወተ-ስጋና ዲሲፕሊን አብረው አይሄዱም ነበር። የፓርቲው ሕግም አይፈቅድም ነበር።

ደራሲዋ የነበራት ፍቅር ድርጂታዊ ሲሆን የአቶ ጌታቸው ደግሞ ወይዘሪቷን መቸና የት እንደሚያገኛት ይከታተል ነበር። ይህ አካሄድ ብዙ ትርምስ እንዳስከተለ ግልጥ ነበር። ለፍትወትና ለነፃነት የትግል ጉዞ አብረው አይሄዱም ነበርና ነው። እምነት ከፍቅር የላቀ መሆኑን ኢሕአፓዎቹ አስመስክረዋል።

## ስለ አንጃና ግድያ

የኢሕአፓ ተልዕኮ፣ ራዕይና አሠራር ግልጥ ሆኖ ሳለ፤ ከዚህ ውጭ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚሠራ አሠራር አንጃነት የተላበሰ ብቻ ሳይሆን አንጃነትም እንደሚፈጥር አያከራክርም ነበር። ዲሞክራሲዊና ዴሞክራሲያዊ የኢሕአፓ ዋና እሴት ከሆኑ እንዴት አድርገው ነው ጌታቸውና ብርሃነ መስቀል በግል አካሄድ እየተወራጡ ግለሰቦችን የሚያነጋግሩና ለማሳመን የሚጥሩ? ደግሞስ በምን ሒሳብ ነበር ብዘኃኑ ያሳለፉት ውሳኔ አንቀበልም የሚሉ። ይኸ አንጃነት ካልሆነ ምን ሊሆን ይችላል? እውነቱን ለመናገር በእንግሊዘኛ ልበለውና "the right of the minority and the rule of the majority" ማለትም "የሕዳጣኑ መብት፣ የብዙኃኑ አገዛዝ" ካልተከበረ እንደሚባለው አቶ ጌታቸውና አቶ ብርሃነ መስቀል ይኸንን እምነትና አሠራር በተግባር ለመቀበላቸው ማስረጃ የለም። በሌላ በኩል ደግሞ የነዚህ ሁለት ግለሰቦች መብት ተነፍጎ ሊሆን ይችላል። እኔ አላውቅም፣ በወቅቱ ማወቅም የለብኝም ነበር። ነገር ግን አንጃው ተፈጠረ በተባለበት ሰዓት በሊጉ (አብዮት) እና በኢሕአፓ (ዴሞ) መካከል መግባባት እንጂ ግጭት እንዳልነበረ በተግባርም ሆነ በንድፈ-ሀሳብ በግልጥ የታወቀ ጉዳይ ነበርና ነው።

ሁሉም እንደሚገነዘበው ብርሃነ መስቀል ኢሕአፓን (ዴሞን) በመዳፉ ውስጥ ለማስገባት፤ ጌታቸው ደግሞ ሊጉን ወይም አብዮትን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ የተታገሉለት ጉዳይ ስለነበር ሁሉም ወጣት ሆነ ሽማግሌ የተገነዘበው ስለነበር ማንም ትኩረት አልሰጠውም ነበር። "ሀ" ና "ለ" ሁነው በቀላሉ ከሰሙ። አሁን

ተመልሰን የምንሰማው "ሀ" ና "ለ" ማጅሪቲ ሆነው ሌሎች ክሊክ (clique) የአብዬን እከክ ወደ እምዬ ልክክ የተባለው እንደገና መደረሱን ነው የሚያሳየው።

ስለ አንጃዎቹ ጠቅላላ አሟሟቱ ጉዳይ ብዙም የሚባል የለም። የሆኖ ሆኖ ግን የጌታቸው አሟሟት አልቧልታ ስለሆነ አልቧልታው ተቀባይነት የሌለው ፓርቲው በአሟሟቱ እንደ የብርሃነ-መስቀል መያዝና ሞት ምንም እጅ ያልነበረበት ስለሆነ በመስለኝ የሚባል አይደለም። ለወሬ ወሬማ ብርሃነመስቀልን ያስያዘችው ሚስቱ ነች ተብሎ አልነበረም። ነገር ግን እውነትነት ያልነበረው መሆኑን በግሌ የምመሰክረው ነው።

የጌታቸው ሞት በርግጥ ያሳዝናል አሟሟቱ ግን የጀግንነት አሟማት አልነበረም። በተለይም ስለ ካራቴ ካነሳን፣የብርሃነ መስቅል ደግሞ የትዕቢት አሟሟት ነበር ብዬ ለመናገር እችላለሁ። እጁን ሲሰጥ የተናገረውንና ያደረገውን ስለማውቅ።

## ስለ መሠረታዊ ልዩነት በኢሕአፓና ኢሕአፓዎች

የመጥሀፉ ደራሲ ወ/ት ሕይወት ከጌታቸውና ከኮምረዱ (ብርሀነመስቀል መሆኑ ነው) እንደተረዳችው ከኢሕአፓ ልዩነት ነበራቸው ብላ ያቀረበቻቸው የሚከተሉት 3 አርእስተ ጉዳዮች ናቸው።

1. ጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት
2. ፋሺዚም በኤትዮጵያ
3. ስለ ግንባር መፍጠር

*ጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት*

የአቶ ጌታቸው በጊሕመ የነበረው አስተሳሰብ ከብዙኃኑ የአመራር አባላት የተለየ ስለመሆኑ ወ/ት ሕይወት ራሷ ተናግራለች። በጌታቸው እምነት ጊሕመ እንደ እስትራተጂ ሳይሆን እንደ ታክቲክና ዘዴ ነበር። በኢሕአፓና በኢሕአፓዎች ግና እንደ ዋና እስትራተጂ ተወስዶ ይኸው እስከ ዛሬ ድረስ እየተፋለሙበት ነው። ጊዚያዊ የሚል ቃል ስለታከለበት ብቻ ለታክቲክ ነበር ለማለት  አያስችልም። ይህ ቃል ቀደም ብሎ በእነ ብርሃነ መስቀል ጊዜ ተማሪዎች እያሉ የሚነሳ ቃል ነበር፣ ንጉሣዊ አገዛዝ ለመተካት ተብሎ የተዘጋጀ መፎክር ነበር። የኤትዮጵያ አብዮት ከተቀማጠለ በኋላ ግን እስትራጂካዊ ሆኖ ቀጠለ። አሁንም እየቀጠለ መሆኑን የሚስተው ያለ አይመስለኝም። ለምስክርነት ከተፈለገ የመጀመሪያ የዴሞክራሲያ እትም እንዲህ ትላለች፣ "አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ"። በኢሕአፓ እምነት ደራሲዋ እንደተረዳችው በእንግሊዘኛ አባባል the end justifies the means - አልነበረም አይደለምም። ይኸኛው እምነት የኤርትራና የትግራይ ታጋዮች መፎክር ሆኖ መኖሩን ለማንም ግልጥ ይመስለኛል። የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጪው የሚለው አነጋገርና በዴሞክራሲያና በሠላም ችሮች ይፈቱ ለየቅል ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝቦች በተግባር አይተዋል ሰምተዋል።

አሁንም ፍትሕና ርትዕ በዴሞክራሲያዊ መንገድ እስከ ጠየቅን ድረስ መፎክሩ ጊዜያዊ ሕዝባዊ ሆኖ ይቀጥላል። የጌታቸው የአብዮት ጥንሰ-ሀሳብና የብርሃነመስቀል

የዲሞክራሲያ ንድፈ-ሀሳብ አልተጣጣሙም ነበር አሁንም ጦሱ እንዳይቀጥል ያስፈራል።

*ስለ ፋሺዝም በኢትዮጵያ*

ፋሺዝም ሲባል ባለ ሦሥት ባሕሪያት የነበረውና ያለው ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ኢ.ሕአፓዎች ሁሌ እንደሚያደርጉት ብዙ ጉዳዮችንና ሐሳቦችን ለውይይትና ለክርክር ያቀርባሉ። የብዙኃኑ መስመር ተከትሎ ወደ ፖሊሲያዊ ሁኔታ ይሸጋገራል። ይኸ ማለት በዴሞክራሲያ መጽሔት ላይ ይሰፍራል። እንግዲህ ከብዙ ውይይቶች፣ ንባብና ክርክር የደርግ ሥራ በተግባር ቁልጭ አድርጎ በተግባር አሳየ። የተደረሰበት የክስተቱ ድምዳሜ እንደሚከተለው ነበር።

1. ፋሺዝም አፈ-ጮሌነት ስለመሆኑ
2. ፋሺዝም በሽብር ስለማመኑ
3. ፋሺዝም ብሔራዊ ስሜትን ከመጠን በላይ ስለሚያኖግደው

ሂትለርና ሙሶሊኒ የተጠቀሙበት ይኸው ዘዴ ነበር። መንግሥቱና ጋዶኞቹ የደገሙት ይህን ነው። መንግሥቱ ሀ. ማርያም እንደነ ሂትለርና ሙሶሉኒ አፈ-ጮሌ አልነበረም እንዳይባል አሰፋ ይርጉ ነበረለት።

*ስለ ግንባር መፍጠር*

ግንባር መፍጠር ባልከፋ ነበር። ተሞክረዋልም፣ ተደርገዋልም፣ እንደ ዕውነቱ ከሆነ አቶ ጌታቸውና አቶ ብርሃነ መስቀል ብቻ ናቸው ግንባር ያልፈጠሩት። በየቅላቸው እኔ ነኝ የወጣት መሪ እኔ ነኝ የግንባሩ መሪ በሚል ተስፋና ቂጭት ብዙ ወጣቶችና ጎረምሶች ለሞት ተዳረጉ።

ደግሞም ደራሲዋ ያላወቀችው ሚስጢር ነበር። እሱም እነ ብርሃነ መስቀል ከደርግ ግንበር ለመፍጠር ያቀረቡት "ፕሮፖዛል" ባለ አምስት የውሳኔ-ሐሳብ ነበር። አሁን አምስቱን ነጥቦች ባላስታውሳቸውም አንደኛውንና የመጨረሻውን ማለት አምስተኛውን በሚገባ አስታውሳሉ።

አንደኛው ኢ.ሕአፓን በከተማ መደምሰስ ሲሆን አምስተኛው ደግሞ የገጠሩን ትግል በሚመለከት ነበር። የነሱን አዲሱን ኢ.ሕአፓ በወይዘሪትዋ ቃንቃ turned EPRP (ግልብጥ) ከሰደደ፣የመንግሥቱ ሀ.ማርያም ድርጅት ቀምተው ግንባሩን ሊመሩ ነበር። መንግሥቱ ግና ጮሌ ስለሆነ የሜዳውን ኢ.ሕአፓ ደምስሳችሁ ጨርሳችኋል ወይ ብሎ ሲጠይቃቸው የመለሱለት ምላሽ እንዲህ ነበር። "እሱማ  እኛ የገጠር አብዮት እንደግፋለን" ሲሉት የሰጣቸውን "የጥፋት ካርድ" ቀምቶ አሽከሮቹን በሉልኝ ብሎ እንዳሳደዳቸው የታወቀ ጉዳይ ነበር።

የገጠሩን ኢ.ሕአፓ ለመበተን ስለአልቻሉ ነበር እንጂ አምነውበት እንዳልነበረ ብዙዎች ይስማሙበታል። ለገጠሩ ኢ.ሕአፓ ምስጋና ይግባውና ከአስራ አንዶቹ አባላት በአንጃነት መከሰስና መገደል በስተቀር ድርጅቱን ከአጠቃላይ ህልውና ማጣት አድነው ይኸው እስከ አሁን ድረስ ለውነተኛው ግንባር እየተዘጋጁ ይገኛሉ።

## ማጠቃለያ

ወ/ት ሕይወት በጋራ ትግል አድጋ በግል የሕዝብ ኑሮን ያወቀች ጀግናና አርአያ ናት። የሰው ባሕሪያት፣ ደጉም ክፉቱንም በወህኒ ቤትና በቀበሌ እስር ቤቶች ተዘዋውራ አይታዋለች። ይኸንን እውነታ ካየች በኃላ ነበር ትግል ውስጥ መግባት የነበረባት ብየ ለራሴ ተናገርኩ።

የፓርቲው አባሎች በውጭ አገር ኑሮውም ሆነ በአገሩ ውስጥ አልፈው ሕይወት ስለ አዩ ያን ሁሉ መስዋዕት ከፍለዋል እየከፈሉም ናቸው። በሌላ አነጋገር የሠራተኛ ማኅበራት፣ የመምህራን፣ የቢሮ የገበሬና የመለዮ ለባሾች ድርጅቶችና አባሎች የኢሕአፓ አባሎችና ደጋፊዎች ናቸው እንጂ የኢሕአወሊ ተከታዮች አልነበሩም። ደራሲዋ በወህኒ ቤትም ሆነ በቀበሎዎች የነበረውን ቅድመ-ሁኔታ አውቀውና ተገንዝበው ነበር በኢሕአፓነት የተሰለፉት። ደራሲዋና የወጣት ሊግ መሠራች ግና ይኸን ሁሉ ሳያዩና ሳያውቁ በንድፈ-ሐሳብ ብቻ ተማርከው ተጋዙ። ስለሆነም ኢሕአፓና ኢሕአፓዎች እንደ ፕሮጀክት ተቆጠሩ።

ኢሕአፓ ፕሮጀክት አልነበረም ሊሆንም አይችልም። የፕሮጀክት ትርጉሙ በሚገባ ካወቅነው።

ከመጽሐፉ ትምህርት ቢገኝ የወህኒ ቤቱና የታሣሪዎች ሁኔታና ትብብር ገለጣዋ ሊያስመሰግናት ይገባል።

Tower in the sky - ላም አለኝ በሰማይ ወተትዋም አላይ ተስማሚ አርዕስት አይደለም እላለሁ። ማንም ግለሰብ ከአብዮቱ (ኢሕአፓዊ አብዮት) በላይ አልነበረም። አሁንም የለም። ኢሕአፓዊ አብዮት ከሌሎች የሚለየው በዚሁ ምክንያት መሆኑ መታወቅ ነበረበት፣ አለበት።

*Some relevant notes for those who read the book "Tower in the sky."*

**On Struggle**

"The struggle was my present, my future, my life" (page 155)

**On Education**

"It did not matter to the Party whether or not I was educated, or so I thought" (page 156)

**On Religion**

I was too busy making history to worry about the existence of God. There was no more need for me to make promise to the Trinity. I knew I could rely on my own resources, the guidance of the League and the Party, and faith in the people. We were the supreme masters of our destiny. Marxism was the lens through which I saw the world." (Page 158)

**On Revolution**

"I often visualized in my mind the 'shining city on the hill', where justice prevailed. That was the "tower in the sky" we had set out to bring down to earth. I would have set the foundation for this "tower" with my blood, flesh and bones if need be. It did not matter if I did not live to see it. What counted was that I fought the great fight then and dedicated my life to the cause. I had no doubt in my mind that we were struggling for a just cause. I believed in my heart and soul and with every fiber of my being that victory would be ours in the end. It was so fulfilling, so promising."(Page 158)

**On her Identity**

"Marxism had become my religion. Marxism brought out the best in me. It gave me hope" (page 157)

Some thoughts for reflections to the benefit of the author of the book, hope was not in the vocabulary of Marxism. That misses the whole essence of struggle. The struggle while on Earth is different from that of the Stars. **የጌታቸውና የሕይወት ኮከብ ተስማሚ ሊሆኑ ይችላሉ። በስማቸውና በተግባራቸው ግና አይጣጣሙም ነበር።** Call me by my name, what is my name?

It is wise to know the *mind* of the Gurages; the *heart* of the Agames and the *body* of the Gondares. That was the role model upon which EPRP was built. Hiwot's mind was revolving on college campus, her heart in Piazza and her body was in Harrarghe province. The sentence of "the struggle was my present, my future, my life" on page 155 was an illusion. It should be replaced by the following sentence "the struggle is my mind, my future is my heart and my life is my Ethiopia."

For comments and questions
oboaradashawl@gmail.com